**መመሪያ ቁጥር________/2016**

**እውቅና ያገኙ ስደተኞችን እና ጥገኝነት ጠያቂዎችን የሥራ መብት አፈጻጸም ለመደንገግ የወጣ መመሪያ**

**መግቢያ**

መንግሥት እውቅና ያገኙ ስደተኞች እና ጥገኝነት ጠያቂዎች የመስራት መብት እንዲኖራቸው በተለያዩ ጊዜያት ቃልኪዳኖችን የገባ በመሆኑ፤

የሀገሪቷ አቅም በሚፈቅደዉ መጠን የስደተኞችን እና ጥገኝነት ጠያቂዎችን አያያዝ ለማሻሻል እና ለችግሮቻቸዉ ዘላቂ መፍትሄ እንዲያገኙ ለማስቻል የተሟላ የህግ ማዕቀፍ ይኖር ዘንድ የስደተኞች ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 1110/2011 የወጣ በመሆኑ፤

እውቅና ያገኙ ስደተኞች እና ጥገኝነት ጠያቂዎች ከተረጂነት ወጥተው ምርታማና ራሳቸውን የቻሉ እንዲሆኑ በስራ ላይ መሰማራት እንዲችሉ በአዋጁ አንቀጽ 26 የተደነገገ ሲሆን፤ ይህንንም ድንጋጌ ለማስፈጸም የሚረዳ መመርያ "ስደተኞች በስራ የሚሰማሩበትን ሁኔታ ለመወሰን የወጣ የአሰራር መመርያ ቁጥር 02/2012" በስደተኞች እና ተመላሾች አገልግሎት ወጥቶ በስራ ላይ መሆኑ፤

ሆኖም አዋጁ ለስደተኞች እና ጥገኝነት ጠያቂዎች እውቅና የሰጣቸው መብቶች አድማስ የቀረበበት ንጽጽር ለውጭ አገር ዜጎች ከተሰጡ መብቶች የተሻለውን ያገኛሉ የሚል ሲሆን ይህንንም ወጥነት እና ዘላቂነት ባለው መልኩ ለመተግበር መመሪያውን ከዚህ መርህ ጋር ማጣጣም አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

ከአዋጁ በፊት ወይም በኋላ የወጡ ህጎች ለአዋጁ መተግበር ያላቸው ሚና ከአዋጁ ድንጋጌዎች ጋር የተጣጣሙ እንዲሆን ማድረግ በማስፍለጉ፤

እነዚህን ዓላማዎች ከግብ ለማድረስ የስደተኞች እና ተመላሾች አገልግሎት በስደተኞች ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 1110/2011 አንቀጽ 46 (2) መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

**ክፍል አንድ**

**ጠቅላላ ድንጋጌዎች**

**1. አጭር ርዕስ**

ይህ መመሪያ "እዉቅና ያገኙ ስደተኞች እና ጥገኝነት ጠያቂዎች የሥራ መብት አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር _____ /2016" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**2. ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1/ **"አዋጅ"** ማለት የስደተኞች ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 1110/2011 ነዉ፤

2/ **"የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ"** ማለት አዋጅ ቁጥር 1156/2011 ነዉ፤

3/ **"የንግድ ሕጎች"** ማለት የንግድ ሕግ አዋጅ ቁጥር 1243/2013 እና የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 980/2008 (እንደተሻሻለው) እንዲሁም በነዚህ ሕጎች መሠረት የወጡና የሚወጡ ደንቦችና መመሪያዎችን ያጠቃልላል፤

4/ **''አሰሪ''** ማለት በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 የተሰጠውን ትርጓሜ የሚይዝ ሆኖ እውቅና ያገኘ ስደተኛ እና ጥገኝነት ጠያቂ አሰሪን ይጨምራል፤

5/ **"የቅጥር ሥራ"** ማለት እውቅና ያገኘ ስደተኛ ወይም ጥገኝነት ጠያቂ በሙያዉ ወይም በጉልበቱ በቋሚነት ወይም በጊዜያዊነት ተቀጥሮ በክፍያ የሚሠራ ነው፡፡

**6/ "የንግድ ስራ"** ማለት ዕውቅና ባገኙ ስደተኞች ወይም ጥገኝነት ጠያቂዎች በተናጥልም ይሁን በጋራ አግባብነት ባላቸው የአገሪቱ ሕጎች መሰረት ከሚመለከታቸው ፈቃድ ሰጪ የመንግስት አካላት ፈቃድ በማውጣት እንደእርሻ፣ ኢንዱስትሪ፣ አነስተኛና ጥቃቅን፣ እደጥበባትና ንግድ በመሳሰሉ ዘርፎች በመሰማራት የሚሰራ ስራ ነው፡፡

